# ***<u>ጩኸቴ</u>!!***

*(አሥራደው ከፈረንሳይ)*



*ኮከብሽ....._..... ኮከቤ:*
*ዕጣዬ....._..... ዕጣሽ ሆኖ፤*
*እኔነቴ ባንቺ:*
*አንቺነትሽ በ’ኔ - አብሮ ተጎናጉኖ፤*

*ትንፋሽሽ ትንፋሼ - ካንድ ሳንባ ሲፈልቅ፤*
*ልቤ አንቺን ሞሽሮ : ሲጠበብ ሲጨነቅ፤*
*አብረን ስንጠመቅ : ባንቺ ወዝ በኔ ላብ፤*
*አንቺ በ’ኔ ፈክተሽ : እኔ ባንቺ ሳብብ፤*
*ቅዠትሽ ቅዠቴ - ሕልሜ ሆኖ ሕልምሽ፤*
*ደስታዬ ደስታሽ - ሃዘኔም ሃዘንሽ፤*
*ጩኸቴ ብቻ ነው: ያልሆነ ጩኸትሽ፤*
*መሰማት ተሰኗቸው: ተደፍነው ጆሮችሽ::*

*ባንቺ አፍ ተጎርሶ - በኔ ጥርስ ሲደቅ፤*
*ተፈጭቶ በኔ ሆድ - ባንቺ አንጀት ሲሰለቅ፤*
*ድው ! ድው ! እያለ - ድንቡልቅ ድንቡልቅ፤*
*ልብሽ ደሙን ሲረጭ : አታሞ ሲደልቅ፤*
*አብሮ ተቀላቅሎ - ደምሽ በደሜ ውስጥ፤*
*ሲፈስ ባንቺ ገላ : የኔን ልብ ሲያቋርጥ፤*
*ተጠላልፎ አንድላይ - አንጀትሽ ካንጀቴ፤*
*ሞትሽ ሆኖ ሞቴ - መኖርሽ ሕይወቴ*
*ጩኸቴ ብቻ ነው : ያልሆነ ጩኸትሽ፤*
*መሰማት ተሰኗቸው : ተደፍነው ጆሮችሽ::*

*ማስታወሻነቷ: ላልተሰሙ ወይም ላልተደመጡ ጩኸቶች በሙሉ !!*